መልእክት አራት

**ባሕላችንን ለመተካት እና በእውነታ አንዱን አዲሱን ሰው ለመሆን**
**እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አዲስ በመሆን**
**በትንሣኤው ሕይወት ትኩስ አቅርቦት**
**ዕለት በዕለት መታደስ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ 2 ቆሮ. 4፡16፤ ኤፌ. 2፡15፤ 4፡22-24፤ ቆላ. 3፡10-11

**I. ኤፌሶን 4፡22 “*ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ*” ይላል፦**

ሀ. *አሮጌው ሰው* የሚያመለክተው በነፍሳችን ውስጥ ያለውን ፍጥረታዊ ሕይወት ነው፤ አሮጌው ሰው በእግዚአብሔር የተፈጠረው እና በኃጢአት የወደቀው ማንነታችን ነው—ሮሜ 6፡6፦

1. አሮጌው ሰው ካካተተው ነገር ሁሉ ጋር ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት ጉዳት ነው፤ አሮጌው ሰው ባለበት ስፍራ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ልትኖር አትችልም፤ ይህ ማለት የሆንነው ነገር፣ ያለን ነገር እና የምናደርገው ነገር የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት የማይቻል ያደርጉታል።
2. በአሮጌው ሰው መሠረት መኖር ከቀጠልን የቤተ ክርስቲያን ሕይወት በከባዱ ይጎዳል፣ አልፎም ይቆማል፤ አሮጌውን ሰው ከፊተኛው የአኗኗር ዘይቤው ጋር ካስወገድን፣ እጹብ-ድንቅ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት፣ ትንሿ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን የሆነ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ይኖረናል፤ እንዲህ ባለ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ክፍፍል ሊኖር አይችልም።

ለ. *ኑሮአችሁን* የሚለው ቃል ታላቅ ነገር ያመለክታል፤ በዓለም ውስጥ ባለ በእያንዳንዱ አገር እና ሕዝብ የተለየ የኑሮ ዘይቤ አለ፦

1. ፊተኛው ኑሮ ከእኛ ጋር የሚገናኘውን ነገር ሁሉ ያካትታል፤ የሆንነውን ነገር ሁሉ፣ የምናደርገውን ነገር ሁሉ እና ያለንን ነገር ሁሉ ማስወገድ አለብን፤ የአኗኗር መንገዳችንን እና ባሕላችንን ማስወገድ አለብን፤ ባሕላችን አብልጦ ጠንካራ በሆነ መጠን አብልጠን ሌሎችን የምንተች እንሆናለን—ተዛ. ኤፌ. 4፡31-32፤ ቆላ. 3፡12-14።
2. ለመታደስ የእውነት ከፈለግን፣ ኑሮአችን (የራሳችንን የአኗኗር ዘይቤ) እና ባሕላችንን የሚያካትተውን ፊተኛ ኑሯችንን ማስወገድ አለብን፤ በአዲሱ ሰው ግሪክ እና አይሁድ፣ አረማዊ እና እስኩቴስ፣ ባሪያ እና ጨዋ ሰው ሊኖሩ አይችሉም፣ ምክንያቱም በእነዚህ ሰዎች መካከል ይገኝ የነበረው ፊተኛ የሕይወት ዘይቤ ተወግዷል።
3. ወደ ፊተኛው ኑሮአችን (የአኗኗር ዘይቤያችን) በተመለስንበት ጊዜ ሁሉ በቅጽበት ውስጣችን እንደጨለመ እና ለእግዚአብሔር ሕይወት እንግዳ እንደሆንን ይሰማናል—ኤፌ 4፡17-19።
4. የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ይኖረን ዘንድ ከተለያዩ ባሕሎች እና አገሮች የመጡ ሰዎች በፊተኛው የሕይወት ዘይቤያቸው አካል የለበሰውን አሮጌውን ሰው ማስወገድ አለባቸው፤ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ስፍራ ያለው ለክርስቶስ ብቻ ነው—ቆላ 3፡10-11።
5. በዜግነት የተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት ተብዬዎቹን ማየት እንዴት ያስከፋል፤ ቅርሳችንን እንደ ውድ ነገር ከመያዝ ይልቅ መተው አለብን፤ ፈጥነን የምንመርጠው አሮጌውን የማሕበረሰብ ኑሯችንን ነው፣ ነገር ግን ኑሮአችን (የሕይወት ዘይቤያችን) በባሕርይ፣ በዘይቤ እና በተግባራዊ ልምምድ ሙሉ በሙሉ አዲስ መሆን አለበት።

**II. በኤፌሶን 2፡15-16 ያለው አዲሱ ሰው ብዙዎች የተካተቱበት ሰው ስለሆነ፣ በ4፡24 ያለውም አዲሱ ሰው ብዙዎች የተካተቱበት ሰው መሆን አለበት፤ በኤፌሶን 4፡24 መሠረት በክርስቶስ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው መልበስ አለብን፦**

ሀ. በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር የተሰቀለውን እና የተቀበረውን አሮጌውን ሰው እናስወግዳለን፤ አዲሱንም ሰው የለበስነውም በጥምቀት ነበር—ቁ. 22-24፤ ሮሜ 6፡6፣ 4።

ለ. አሮጌውን ሰው ማስወገድ እና አዲሱን ሰው መልበስ የተፈጸሙ ሃቆች ናቸው፤ አሁን በአእምሯችን መንፈስ በመታደስ እነዚህን ሃቆች መለማመድ እና እውን ማድረግ አለብን—ኤፌ 4፡23፦

1. አሮጌውን ሰው ማስወገድ መስቀሉን በእኔነት ላይ በመተግበር አሮጌውን ማንነታችንን መካድ እና በፈቃድ መተው ነው—ቁ. 22፤ ማቴ. 16፡24።
2. አዲሱን ሰው መልበስ በተትረፈረፈው የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ክርስቶስን መኖር እና ማጉላት ነው (ፊልጵ. 1፡19-21)፤ ይህ አዲሱን ሰው በመፍጠር ክርስቶስ ያከናወነውን ነገር መተግበር ነው (ኤፌ. 2፡15፤ 4፡24)።

ሐ. ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የተዋሐደው መንፈሳችን የአእምሯችን መንፈስ መሆን አለበት (ቁ. 23)፤ ከዚያ በኋላ ኑሯችን በሙሉ በመንፈስ ይሆናል፣ የምናደርገውም ነገር ሁሉ በመንፈስ መሠረት ይሆናል፤ በዚህ መንፈስ ስንታደስ አዲሱን ሰው እንለብሳለን።

መ. ወደ አእምሯችን እየተሰራጨና አእምሯችንን እየሞላ ባለው በተዋሐደው መንፈስ መሠረት መመላለስ አለብን፤ በዚህ መንገድ የአዲሱ ሰው የዕለት ዕለት ምልልስ በአእምሮ መንፈስ ይሆናል፤ ይህ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ምሥጢር ነው—ቁ. 23።

ሠ. አዲሱ ሰው ያለው በመንፈሳችን ውስጥ ነው፤ አዲሱን ሰው የመልበሻው መንገድ እግዚአብሔር፣ የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ እና አዲሱ ሰው የሚገኙበት መንፈሳችን (ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የተዋሐደው) የአእምሯችን መንፈስ ሲሆን ነው—2፡22፤ 4፡23፡-

1. መንፈስ የአእምሯችን መንፈስ ይሆናል ማለት መንፈስ ለአእምሯችን አቅጣጫ ይሰጣል፣ አእምሯችንን ይቆጣጠራል፣ የበላዩ ይሆናል፣ አካሄዱን ያግዳል እና አእምሯችንን ይይዛል ማለት ነው (ተዛ. 1 ቆሮ. 2፡15-16፤ 2 ቆሮ. 2፡13፤ 10፡4-5)፤ መንፈስ አእምሯችንን አቅጣጫ ሲያስይዘው ማንነታችንን በሙሉ በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ይሆናል።
2. አዲሱን ሰው የምንለብስበት መጠን መንፈሳችን ማንነታችንን አቅጣጫ በሚያስይዝበት መጠን ይወሰናል (1 ቆሮ. 2፡15)፤ መንፈሳችን የበላያችን ሲሆን እና አቅጣጫ ሲያስይዘን ለባሕል፣ ለአስተሳሰባችን ወይም ለድንጋጌዎች (ለሕግ ትዕዛዛት) ምንም ስፍራ አይኖርም፤ ማንነታችን በሙሉ በመንፈሳችን የበላይነት፣ ቁጥጥር፣ መግዛት እና አቅጣጫ ሥር ስለሚሆን ለገዛ መንገዳችን ምንም ክፍል አይኖርም።
3. የተዋሐደው መንፈስ አእምሯችንን አብልጦ በሰረጸ፣ ፈጽሞ በሞላ እና በያዘ መጠን የክርስቶስ አእምሮ አእምሯችን ይሆን ዘንድ የበለጠ እንፈቅዳለን—ፊልጵ. 2፡5፤ 1 ቆሮ. 2፡16፤ ሮሜ 12፡2።

ረ. በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን እንደተጠናቀቀ ውጤት ሕይወት የሚሰጠው መንፈስ አዲሱን ሰው ይዞ ወደ መንፈሳችን ውስጥ ገባ፤ አሁን አዲሱ ሰው ማንነታችንን በሙሉ ፈጽሞ መሙላት እና ወደ ማንነታችን ክፍል ሁሉ መሰራጨት አለበት፤ ይህ መሰራጨት አዲሱን ሰው መልበስ፣ መታደስም ነው።

ሰ. በአእምሯችን መንፈስ እንጂ በአእምሯችን ከንቱነት መኖር የለብንም፤ ይህ ብዙዎችን ለተካተቱበት አንዱ አዲሱ ሰው የየዕለት ኑሮ ቁልፍ፣ በእግዚአብሔር ባሕሪ፣ በክርስቶስ መዓዛ እና በመንፈስ አንድነት የተሞላ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እንዲኖረን ምሥጢሩ ነው—ኤፌ. 4፡3-4፣ 17-18፣ 23-24።

ሸ. ጌታን በመውደዳችን እና ዕለት ዕለት በጸሎት እና ቃሉን በማንበብ በመንፈሳችን እንቅስቃሴ አእምሯችን በተዋሐደው መንፈስ ይሞላል፤ ይህ አእምሯችንን ይለውጣል ያድሰውማል፤ በአእምሯችን መታደሳችን ትርጉሙ የስብዕና ሕይወት የሚመለከቱትን ነገሮች አሮጌ ጽንሰ-ሃሳቦቻችንን ማስወገድ፣ እና በቅዱስ መጻሕፍት ትምህርት እና በመንፈስ ቅዱስ አብርሆት አዲስ መደረግ ነው—መዝ. 119፡105፣ 130፤ 2 ጢሞ. 3፡15-17፤ ዘዳ. 17፡18-20።

ቀ. በዚህ ዘመን የእግዚአብሔር ዓላማ የመፈጸሙ፣ አንዱን አዲሱ ሰው በእውነታ የማግኘት ብቸኛው አማራጭ ሁላችንም በአእምሯችን መንፈስ ለመታደስ ፈቃደኞች ከሆንን ነው።

**III. ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች [የተናገረው] ቃል ማዕከላዊው ነጥብ የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አእምሮ ይመለከታል፤ አዲሱ ሰው የተፈጠረው በመንፈሳችን ውስጥ ነበር ፣ እና ሙሉ እውቀትን ለማግኘት በክርስቶስ መልክ መሠረት በአእምሮአችን ውስጥ እየታደሰ ነው—ኤፌ. 2፡15፤ ቆላ. 3፡10-11፡-**

ሀ. አዲሱ ሰው የአሮጌው ፍጥረት ከነበርነው ከእኛ ስለተፈጠረ መታደስ ያስፈልገዋል፤ *ሙሉ እውቀት ለማግኘት* በሚለው ሃረግ እንደተመለከተው ይህ መታደስ በዋነኛነት የሚከናወነው በአእምሯችን ነው—ቁ. 10።

ለ. በእግዚአብሔር መሠረት የሆነው የአዲሱ ሰው መፈጠር ተፈጽሟል፣ ነገር ግን በልምምዳችን አዲሱ ሰው ወደ ሙሉ እውቀት ጥቂት በጥቂት እየታደሰ ነው፤ አዲሱን ሰው አብልጠን በለበስን መጠን አብልጠን እግዚአብሔር በሆነው መሠረት እንታደሳለን፣ እና አብልጠን መልኩን፣ እርሱ የሆነውን መገለጥ እንይዛለን—ቁ. 10።

ሐ. መታደስ አሮጌውን ንጥረ-ነገር ለመተካት እና ለማስወገድ የእግዚአብሔር ንጥረ-ነገር ወደ ማንነታችን ውስጥ ሲጨመር ነው—ራእ. 21፡5፤ 2 ቆሮ. 5፡17፤ ሮሜ 12፡2፤ 2 ቆሮ. 4፡16፡-

1. ፍጥረታዊው እና ብሔራዊው አስተሳሰባችን በዘራችን እና በባሕላዊው አመጣጣችን መሠረት የተማረ እና የተገነባ ነው፤ ይህ ለአዲሱ ሰው ተግባራዊ ሕልውና ታላቅ መሰናክል ነው።
2. አንዱ አዲሱ ሰው ወደ ሙሉ ሕልውና ይመጣ ዘንድ በብሔራዊ እና ባሕላዊ አመጣጣችን የተገነባውን አእምሮ ጥልቅ-ዝርዝር-ሙሉ መታደስ መለማመድ አለብን።

መ. አዲስነት እግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህ አዲስ መሆን በሕይወት እና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር መሆን ነው፡-

1. እግዚአብሔር ለዘላለም አዲስ ነው፣ እና መላው ማንነታችንን ለማደስ ለዘላለም አዲስ የሆነውን ውስጠ-ነገሩን ወደ ማንነታችን ውስጥ ያሰርጻል—ሮሜ 12፡2፤ ቆላ. 3፡10።
2. የእግዚአብሔር መንፈስ፣ ለዘላለም አዲስ በሆኑት እና ፈጽሞ ሊያረጁ በማይችሉት፣ እና ለዘላለም በሚኖሩት እና በማይለወጡት የእግዚአብሔር ባሕርያት የውስጥ ክፍሎቻችን በመስረጽ ያድሰናል—ራእ. 21፡5።
3. የሚያድሰው መንፈስ እኛን አዲስ ፍጥረት፣ አዲሱን ሰው ለማድረግ መለኮታዊውን ውስጠ-ነገር ወደ ማንነታችን ውስጥ ያካፍላል—ቲቶ 3፡5፤ 2 ቆሮ. 5፡17፤ ገላ. 6፡15።

## IV. ባሕላችንን ለመተካት እና እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አዲስ በመሆን በእውነታ አንዱን አዲሱ ሰው ለመሆን ትኩስ በሆነው የመለኮታዊው ሕይወት አቅርቦት ዕለት ዕለት የሚታደሱ ሰዎች መሆን ያስፈልገናል—2 ቆሮ. 4፡16፡-

ሀ. አዲሱን ሰው መልበስ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ አይከናወንም፤ በተቃራኒው በክርስቲያን ሕይወታችን በሙሉ የሚቀጥል የሕይወት ዘመን ሁሉ ጉዳይ፣ አዝጋሚ ሂደት ነው።

ለ. እኛ፣ ዳግም የተወለድን አማኞች እንደ አዲሱ ሰው ክፍል በመለኮታዊው ሕይወት አዲስነት በትንሣኤው ሕይወት መመላለስ እና በመንፈስ አዲስነት ማገልገል አለብን—ሮሜ 6፡4፤ 7፡6።

ሐ. አማኞች በሙሉ በሕይወት አዲስነት በመመላለስ (6፡4) አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን እየሆኑ እና በመንፈስ አዲስነት በማገልገል (7፡6) አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን እየገነቡ ስለሆነ እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አዲስ ይሆኑ ዘንድ መታደስ አለባቸው።

መ. በአእምሯችን መንፈስ መታደሳችን በከባቢ ሁኔታችን ውስጥ ባለው መከራ የውጫዊው ሰው መጥፋት በኩል ለውስጥ ሰውነታችን መታደስ ወደ ክርስቶስ መልክ የዕለት ተዕለት መታደሳችን ነው—2 ቆሮ. 4፡16፡-

1. በመከራ ውስጥ ሳለን መታደስን መቀበል አለብን፤ አለበለዚያ የምናልፍበት መከራ ለእኛ ምንም ትርጉም አይኖረውም፤ በውስጣችን መሸሸጊያ አለ—መንፈሳችን—መዝ. 91፡1፤ 27፡5፤ 31፡20፤ ኢሳ. 32፡2፤ 2 ጢሞ. 4፡22፤ ገላ. 6፡17-18።
2. ጥቂት በጥቂት እና ዕለት በዕለት የውጭ ሰውነታችን እንዲጠፋና ትኩስ በሆነው እስትንፋሳዊው ክርስቶስ እንደ ትንሣኤ ሕይወት የውስጥ ሰውነታችን እንዲታደስ እግዚአብሔር ከባቢ ሁኔታችንን ያዘገጃጃል—2 ቆሮ. 4፡16።

ሠ. ዕለት ዕለት ለመታደስ በየማለዳው መነቃቃት ያስፈልገናል—ማቴ. 13፡43፤ ሉቃ. 1፡78-79፤ ምሳ. 4፡18፤ መሣ. 5፡31፤ 2 ቆሮ. 4፡16።

ረ. ዕለት ዕለት የምንታደሰው በአራት ነገሮች ነው፡- በመስቀሉ (ቁ. 10-12)፤ በመለኮታዊው ሕይወት እንደገና በምንታደስበት፣ በምንሠራበት እና በምንዋቀርበት በመንፈስ ቅዱስ (ቲቶ 3፡5)፤ በተዋሐደው መንፈሳችን (ኤፌ. 4፡23)፤ እና በቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል (5፡26)።

ሰ. ወደ ጌታ ማዕድ በአዲስነት መምጣት አለብን (ማቴ. 26፡29)፤ ጌታ ያረጀ ማዕድ ፈጽሞ አይቀበልም፤ “ይቅርታ፤ ይቅር በለኝ (ይቅር በይኝ)” ማለትን በመማር መታደስ ያስፈልገናል።

## V. የአዲሱ ሰው መታደስ የሚመረኮዘው ከላይ ያሉትን ነገሮች በመፈለጋችን ላይ ነው—ቆላ. 3፡1-2፤ ኤፌ. 2፡5-6፡-

ሀ. ከላይ ያሉትን ነገሮች መሻት በሰማያዊ አገልግሎቱ ለክርስቶስ እንቅስቃሴዎች ምላሽ መስጠት እና አገልግሎቱን ማንጸባረቅ ነው—ዕብ. 2፡17፤ 4፡14፤ 7፡26፤ 8፡1-2፤ ራእ. 5፡6፤ ቆላ. 3፡1-2፡-

1. በመንፈሳችን ውስጥ ባለው ሁሉን-ባካተተው መንፈስ በኩል በሰማይ ካለው ክርስቶስ በምድር ወዳለነው እኛ ስርጭት አለ—ኤፌ. 1፡19፣ 22-23፤ 2፡22፡-
   - ሀ. የመለኮታዊው ስርጭት ተቀባይ መንፈሳችን ነው፣ በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር ዙፋን ደግሞ የስርጭቱ መነሻ ነው—ራእ. 5፡6።
   - ለ. ወደ መንፈሳችን በመዞር ወደ ሰማይ ከፍ እንደረጋለን፤ በሰማይ ከእግዚአብሔር ዙፋን ወደ መንፈሳችን ውስጥ ካለው ስርጭት የተነሣ ክርስቶስን እዚህ በምድር ላይ ስንለማመደው እና ስንደሰተው በተመሳሳይ ጊዜ በሰማይ ነን—4፡1-2።
2. በሰማያዊ አገልግሎቱ ክርስቶስ ሰዎችን በእረኝነት እየንተንከባከበ ነው፣ እኛም ሰዎችን በእረኝነት በመንከባከብ ከእርሱ ጋር መተባበር አለብን፤ ይህን ኅብረት ከተቀበልን ጌታን መልሶ የሚያመጣ ትልቅ መነቃቃት በምድር ላይ ይሆናል—1 ጴጥ. 5፡1-4፤ ተዛ. ማቴ. 9፡36፤ 10፡1-6፤ ዮሐ. 21፡15-17፤ 1 ጴጥ. 2፡25፤ ዕብ. 13፡20።

ለ. ከእንቅስቃሴዎቹ ሁሉ ጋር ወደ ሰማያዊው ክርስቶስ ከዞርን እና በእነዚህ ነገሮች ላይ አእምሯችንን ከተከልን የአዲሱ ሰው መታደስ በቅጽበት ይከናወናል—8፡1-2፤ 12፡2፤ ቆላ. 3፡2።

ሐ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ፣ አማኞችን እንደ አዲሱ ፍጥረት አዲሱን ሰው ማድረግ የሆነውን የእግዚአብሔርን ውጥን ያጠናቅቃል፤ አዲሱ ሰው እንደ የእግዚአብሔር ድንቅ የጥበብ ሥራ በአጽናፍ-ዓለም ሙሉ በሙሉ አዲስ ነገር፣ የእግዚአብሔር አዲስ ፈጠራ ነው—ቁ. 10-11፤ 2 ቆሮ. 5፡17፤ ገላ. 6፡15-17፤ ኤፌ. 2፡10፣15።

መ. የእግዚአብሔር ግብ በስተመጨረሻ የአንዱ አዲስ ሰው የመጨረሻ መደምደሚያ የምትሆነውን አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን የሚያጠናቅቀውን አንዱን አዲሱን ሰው ማግኘት ነው።

© 2020 Living Stream Ministry